# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 40 የካቲት 12 2001 ዓ.ም


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

... **ለራሱ ህገ-መንግስቱን እየሰበረ ህጋዊ እና ሰላማዊ ተቃውሞ የሚያደርጉ ዜጎችን ግን ጸረ-ህገ መንግስት ብሎ በመፈረጅ ለህገ-መንግስቱ ያለውን ንቀት ከመግለጽም አልፎ ደጋግሞ አፊዞበታል።**

## የኢትዮጵያው መንግስት ሰራተኛ:- ዋና ግፍ ቀማሽ እና ታላቅ የለውጥ ሃይል

*በተሰፋዬ ማሩ*

በገጽ 3 ላይ ይመልከቱ

## ማስታወቂያ

ዛሬ በግንቦት7 ንቅናቄ ውስጥ የተሰባሰብነው ግለሰቦች ሃገራችን ወደሌላ የአመጽ አዙሪት እንዳትገባ ከምር ተጨንቀን፣ አንቸኩል! ለወያኔ እድል እንስጠው፤ ግድ የላችሁም እነዚህ ሰዎች የእዚችው ሃገር ዜጎች ናቸው ውለው አድረው ለሀገራችን በጎ መመኘታቸው አይቀረም ብለን ብዙዎች እስከሚታዘቡን መሟገታችንን ----ያውቃሉ?

ሽህ ግዜ ቀናውን፣ ሽህ ግዜ የሰላሙን መንገድ ብንመኘው፣ ሽህ ግዜ እረ ተው፣ ይህች ሃገርና ሁላችንም በጥፋት አዙሪት ውስጥ መድፈቁ ይብቃን ብለን ብንማጸን፤ ከእዚህም አልፎ ተርፎ በታሪካችን አድርገን የማናውቀውን፣ ለሰላም ካለን ጽኑ ፍላጎት ተነስተን፣ በሃገራችን ላይ የተሰራውን በደል ወደ ጎን አድርገን፣ በነጻነታችን ተደራድረን ለእረቅ ለስምምነት ጉሮሯችን እስኪደርቅ በመወትወታችን ፣ ከመለስ ዜናዊና ከጓደኞቹ ያገኘነው ምላሽ፣ እየገዘፈ የሚሄድ ዘረኛነት እብሪትና ንቀት እንደሆነ እርስዎስ ቢሆን ሳይታዘቡት አይቀርም፡፡

እነዚህ ዘረኛ እብሪተኞች ትእግስታችንና ተማጽናችንን ከፍርሀት የሚቆጥር፣ ያለእኛ ደፋር የለም አንዲሉ አድርጎ የሚያይ በባሩድ ሽታ የሰከረ ህሊና ያላቸው መሆናቸውን እርስዎም እንደኛ ሳይረዱት አይቀርም፡፡

በተደጋጋሚ ኢትዮጵያዊ ስሜት ያላቸውን ዜጎች ማስቃየት ማዋረድና ማዋከብ ስራ ብለው ተያይዘውታል፡፡ የቅረቡ ሰለባቸው ቴዲ አፍሮ የሆነበት ምክንያት የሚነሳው ከእዚሁ ለኢትዮጵያ ካላቸው ጥላቻ ነው፡፡ በልምና በምልጃ ስለሰላምና እርቅ በመስበክ የለየላቸው አረመኔዎችን ወደ ቀና ጎዳና መመለስ ይቻላል ብለን እኛ በግነብት ሰባት ውስጥ የተሰባሰብን ወገኖዎችዎ አናምንም፡፡ ይህንን እምነታችንን የሚጋሩ ከሆነ! ይነሱ ይቁሙ እኔንም በቃኝ ውርደት ብለው ከቆሙቱ ጎን ቁጠሩኝ ይበሉ፡፡

የግንቦት7 ንቅናቄን ሁሉ ገብ ትግል ይደግፉ፡፡ ለእዚህ ትግል ማራመጃ ግንቦት ሰባት ይሆን ዘንድ ግንቦት 7 የጀመረውን የገንዝብ ማሰባሰብ ስራ ያግዙ፡፡ ሌላውም እንዲተባበር ያስተባብሩ፡፡

ግንቦት 7 ለፍህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ

## ታላቅ ህዝባዊ ስብሰባ በሲያትል

የግንቦት ሰባት አመራር አባላት የሆኑት ዶ/ር ብርሀኑ ነጋና አቶ ሙሉነህ እዩኤል ቅዳሜ ፌብሩዋሪ 14 ቀን በየስለር ኮሚኒቲ ሴንተር ከሲያትልና ካካባቢው ከመጡ በርካታ ኢትዮጵያውያን ጋር ከወያኔ/ኢሕአዴግ መውደቅ በኋላ በሚከሰተው የኢትዮጵያ የወደፊት ሁኔታ ላይ ሰፊ ውይይት አደረጉ። ስብሰባው ከቫንኩቨር በመጣው በቀድሞው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ፕሬዜዳንት ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በወጣቶችና የ1997ን ምርጫ በተሳተፉና በአገራቸው ህዝብ በምርጫ የሰጠውን ድምጽ አይን በአወጡ ወሮበሎች መነጠቁ ያንገበገባቸው ብዙ ታዳሚዎች የተገኙበት ነበር።

ስብሰባው በሰከነ መንፈስ የተካሄደ ሲሆን የወያኔ ቡድን በአስቸኳይ በመውረዱ አስፈላጊነት ላይና ዲሞክራሲያዊ ስርአት ማስፈን በሚቻልበት ሁኔታ ስምምነት ላይ በመድረስ የተጠናቀቀ መሆኑ ተጠቅሷል። ከስብሰባው በኋላ ተሰብሳቢው በተዘጋጀው የራት ግብዣ ላይ በመገኘት ለንቅናቄው ድጋፍ የሚውል ከፍተኛ ገንዘብ ማሰባሰብ መቻሉንም ዘጋቢያችን ጠቅሶልናል።

## የመለስ ዜናዊ የስልጣን እለቃለሁ ዛቻ

መለስ ዜናዊ ከ2002 ምርጫ በኋላ በጠቅላይ ሚኒስትርነት ላልቀጥል እችላለሁ፣ የመቀጠሉንና ያለመቀጠሉን ውሳኔ ሰጭው ግን ፓርቲዬ ነው በማለት የተለመደውን ቲያትር ባላፈው ዓርብ መሥራቱን ከሥፍራው ተዘገበ።

መለስ ዜናዊ ባለፈው አርብ በአዲስ አበባ የሚገኙትን ጋዜጠኞች ሰብስቦ ከ2002 ምርጫ በኋላ በጠቅላይ ሚኒስትርነት የመቀጠል ፍላጎት እንደሌለው መግለጫ በሰጠበት አፉ መልሶ ይህንን ያለመቀጠል ፍላጎቴ ተፈጻሚ የሚሆነው በድርጅቴ ውሳኔ ነው በማለት፣ ኢህአዴግ የሚባለው በእውነቱ ግን በዋንኛነት በወያኔና በተለይ በመለስ ዜናዊ የሚዘወረውና በዙሪያው ተለጣፊዎችን የኮለኮለው ድርጅት ለውሳኔው ሃላፊ እንደሚሆን አድርጎ አስቀምጦታል። የመለስ ዜናዊንና የኢህአዴግን ግንኙነት በሚመለከት ባለፉት 18 አመታት በቂ እውቀት ያካበተው የኢትዮጵያ ህዝብ ግን በመለስ ዜናዊ ንገግር ውስጥ የተረገዘውን ለበጣ የሳተው አይመስልም። ህዝቡም የመለስን ንግግር ያዳመጠው "ሰውየው ያሾፋል አንዴ?" በሚል ስሜት እንደሆነ የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ካሰባሰበው አስተያየት ለመረዳት ተችሏል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## "የኢትዮ-ሶማሊያ ጦርነት አክራሪዎች እንዲስፋፉ አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል"

### *የሲ.አይ.ኤ ዳይሬክተር በኢትዮጵያ*

የሲ አይ ኤው ተሰናባች ዳይሬክተር ወያኔ ሶማሊያን መውረሩን የእስልምና አክራሪዎች እንደትልቅ መቀስቀሻ መጠቀማቸው እና ለአላማቸው ማስፈጸሚያ ማዋላቸውን ገልጸዋል።በርካታ ተማሪዎች በተለይ ከለንደን በጊዜው የሙስሊም አክራሪ ቡድኖችን እንደሚቀላቀሉ ሲዝቱ እንደነበር በተለይ ባለፈው አመት ጥቅምት የኦክፎርድ ዩኒቨርሲቲ የቢዝነስ ተማሪ የነበረ የ21 አመት ወጣት በኬንያ አድርጎ ሶማሊያ ገብቶ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የነበሩበት አካባቢ ቦምብ አፈንድቶ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሳይጎዱ ቢያመልጡም ከ20በላይ የወያኔ ወታደሮች በፍንዳታው መሞታቸው ይታወሳል።ይሄው አክራሪ "ሁላችሁም ወደ ሶማሊያ መጥታችሁ ጠላታችሁን ተፋለሙ" የሚል መልእክት ከመሞቱ በፊት አስቀምጦ እንደነበረ ታውቋል።

በታሪኳ አንድም ጊዜ ጎረቤቶቿን ወራ የማታውቅ ጥንታዊት ሀገር ዛሬ በወያኔ አዝማችነት በሶማሊያ ላይ የተፈጸመው ወረራ የህዝቧን ምሬት እጥፍ እንዳደረገው ይታወቃል።የሀገሪቱን ንብረት እና በተራቡ ምንዱባን ዜጎች ተለምኖ የመጣን ገንዘብ ትርጉም ለሌለው ብቻ ሳይሆን ሀገሪቱን በበርካቶች ጥርስ ውስጥ ላስገባ ወረራ ያዋለው ወያኔ፤ ያተረፈልን የእነኦሳማ ቢላደንን ዛቻ ነው ይላሉ ታዛቢዎች።

የወያኔ ጦር በአሸማቃቂ ሽንፈት ከሶማሊያ ቢወጣም ተመልሶ ወደ ሶማሊያ እየገባ እንደሆነ የጎሳ መሪዎች እና የሀገሬው ሰዎች እየተናገሩ ነው።ችች

# የየካቲት አብዮትን 35ኛ አመት ለማስታወስ

የካቲት 11 ቀን በግብታዊነት የተቀሰቀሰው ህዝባዊ አመፅ፣ እነሆ በዛሬው እለት 35ኛ አመት ሞላው ። በነዚህ 35 አመታት ኢትዮጵያችን ከፍፁማዊ ዘውዳዊ አገዛዝ በመጀመሪያ ወደ ወታደራዊ አምባገነንነት ቀጥሎም ወደ ዘረኛ አድሎአዊ አገዛዝ ተሸጋግራለች ። ከየካቲት በፊት የግለሰብ መልከኞችና ጉልተኞች ተጠማኝ የነበረው ገባር፣ ባለፉት 35 አመታት የመንግስት ስልጣን የያዙ አምባገነኖች ጭሰኛ ሆኗል ። በከተማም በገጠርም የሃብት ባለቤትነት በመንግስት መልካም ፈቃድ በኪራይ የሚገኝ ተደርጓል ። የሃገራችን አንድነት ከምንጊዜም በላይ በአስጊ ሁኔታ ውስጥ ወድቋል ። ኤርትራ ተገንጥላለች ፣ በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይ ኢትዮጰያዊነታቸውን አምረው እንዲጠሉ ለማድረግ የታቀደ ብካይና አበሳ እየተካሄደ ነው ። ዜጎች የዘርና የዘውግ ጀርባቸው ወንጀል ሆኖ፣ ጋምቤላውም አማራውም፣ አኙዋኩ ጋሞው፣ ሲዳማው ሃድያው ሁሉም ተራ በተራ፣ በተናጠልና በጋራ ይታረዳል፤ ይታሰራል፤ ይጋዛል፤ ይሰደዳል:: ኦሮሞነት እንደ ወንጀል የተቆጠረ ያህል፣ እስር ቤቱ ኦሮሙኛ መናገር ጀምሯል ።

ሃገሬው ካልተመጣጠነ በቀን ሁለቴ ከመመገብ፣ በቀን አንዴ እንዲያውም በባሰባቸው ቤተሰቦች ውስጥ በፈረቃ መብላትና መተኛት ተጀምሯል ። ይህ እንግዲህ በአስር ሚሊዩኖች የሚራበውን፣ ለዘመኑ ገዥዎች ከቁጥር ጨዋታነት በላይ ትርጉም የሌለውን በቀን አንዴ መመገብ አቅቶት በቸነፈር ገደል ላይ የተንጠለጠለውን ወገናችንን ሳይጨምር ነው :: በተስፋ መቁረጥም ጫት፣ አደንዛዥ እፅ፣ ዝሙትና ስደት የወጣቱ አይነተኛ መገለጫ እንዲሆን ተደርጓል ። ይህን አስከፊ እውነታ የተጋፈጠው ዜጋ፣ እንዴት ነው ከእዚህ የብካይና የአበሳ አዙሪት ውስጥ የወደቅነው፤ ለምንስ ነው ከእዚህ አዙሪት መውጣት ያልቻልነው የሚል ጥያቄ በምሬት ያነሳል:: አንዳንድ ወገኖች ለእዚህ ዜጎች ባሁኑ ወቅት ለሚገኙበት አስከፊ ሁኔታ መነሻውና ምክንያቱ ዛሬ 35ኛ አመቱን የምናከብረውን አብዮት ይላሉ። ይህ አመለካከት በተለይ የ66ቱን አብዮት ሲቀሰቀስ በቦታው ባልነበረው ወይም ህጻን በነበሩት ወጣትና ጎልማሶች መሃል የገረረ ነው::

ለምን የየካቲት አብዮት ፈነዳ? የየካቲት ህልምስ ምን ነበር? የህዝባችን ህልም ከተራራው አናት መውጣት አቅቶት እንዴት ከሸለቆው ውስጥ ተዳፈነ? ምን ይሻላል? እነዚህ ጥያቄዎች ጥናትና ምርምርን የሚሹ፣ መፃህፍትን የሚያስፅፉ መሰረታውያን ናቸው ። የካቲትን ለመዘከር ያህል ግን በደምሳሳው እንነካካቸዋለን ። የካቲትን የወለደው ጭቆና ነው ። የመሬት ረሃብ ነው ። የዴሞክራሲያዊ መብቶች መነፈግ ነው ። የብሄረሰብ እኩልነት ጥማት ነው ። በአፄው ዘመን ለእነዚህ ሁሉ ችግሮች መፍትሄ የሚፈልግላቸው አልነበረም:: "ገባር የሚበላው እንጂ የሚገብረው አያጣም" እየተሾፈበት፣ አንገቱን ደፍቶ የኖረው የመሬት ረሃብተኛ "እምቢ ለእንጀራዬ" ያለ ቀን፣ ሊገታው የሚችል ጦር ሊገኝ አልተቻለም ። የገበሬው ልጅ የነበረው ወጥቶ አደር (ወታደር) ራሱ፣ ባስታጠቁት ጌቶቹ ላይ ሲያምፅ፣ ያኔ የፍፃሜው መጀመሪያም ሆነ።

በምድር ላይ የመለኮት ወኪል ነኝ ይል በነበረው ዘውድ አገዛዝ ላይ፣ "ምድራዊ ውክልናን ከኛ ሳታገኝ ልትገዛን አትችልም - ህዝባዊ መንግስት ይቋቋም" ተፈከረበት ። ሼሁና ቀሳውስቱ ሳይቀሩ በየአደባባዩ ተመሙ ። የመንግስት ጋዜጦች ከእስር ነፃ ወጥተው፣ የህዝቡን ዋይታ ያስተጋቡ ጀመር ። ያለመንግስትና ፖሊስ ፈቃድ መሰብሰብና ትዕይንተ ህዝብ ማድረግ፣ የኢትዮጵያ ዜጎች ዕለታዊ ተግባር ሆነ ። ሃገሬው በልመናና በህጋዊ መንገድ ማግኘት ያቃተውን መብቱን በአመፅ ያገኘ ዘንድ አማራጭ አልነበረውም ። ለመብቱም ሲል ከዳር እስከ ዳር እንደ አንድ ሰው አስገመገመ ። ታክሲዎች፣ የማዘጋጃ ቤት የፅዳት ሰራተኞች፣ ተማሪዎች የስራ ማቆም አድማ ሲጠሩ፣ የሰራተኛው ማህበር ሃገር አቀፍ አድማ ለማድረግ ተባበረ ። ከዚያ በኋላ የካቢኔ መለዋወጥ እንኳ አጥጋቢ ሊሆን አልቻለም ። በወታደርና በቀሳውስት ድጋፍ የቆመ ስርአት የሁለቱንም ምርኩዝ ሲያጣ፣ ራሱን ችሎ መቆም ተሳነው ። "የወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛበታል" እንዲሉ፣ የስርአቱ ደካማነት ከተጋለጠ በሁዋላ፣ የሰከረ አሳ ለማስገር መረቡን የሚወረውረው ዜጋ ቁጥሩ እየጨመረ፣ ንዴቱ እየጋመ፣ ጥያቄው እየተወሳሰበ፣ የየካቲት አብዮትን ወለደ::

ሆኖም ኢትዮጵያውያን እንደ ህልማቸው ካሰቡት ለመድረስ አልተቻላቸውም ። ድርጅትና አመራር ያንሳቸው ነበር ። ስለሆነም፣ ይበልጥ በተደራጀው የምርጥ መኮንኖች ደርግ የትግል ፍሬአቸው ተበላ ። አብዮቱም ተቀለበሰ ። የህዝብ ልጆችም የቀይ ሽብር ሰለባ ሆኑ ። ኢትዮጵያችን እንደ ፈረንሳይ፣ አሜሪካ፣ ሩስያና ቻይና ሁለንተናዊ የማህበራዊ ለውጥ ለማምጣት አብዮት ለማካሄድ ከቻሉት ሃገሮች መመደብ ብትችልም፣ የኢትዮጵያ አብዮት እንደእነዚህ ሀገራት አብዮቶች የተሸከመውን ራእይ በሙሉ ወይም በከፊል ከግቡ ማድረስ ሳይችል በመቅረቱ ትርጉሙ ደበዘዘ:: በእዚህ አብዮት ውስጥ ህዝብ የከፈለው መስዋእትነት፣ ችግር ባልነበረበት ችግር ፈጥሮ ወደ ባሰ ችግር እንደጨመረን አድርገው የሚያቀርቡት ቁጥራቸው ተበራከተ:: አብዮቱ እርባና የሌለው፣ አላስፈላጊ ትርምስና ቀውስ እንዳስከተለ ተደርጎ እንዲወሰድ ሆነ:: ይሁንና ይህ አመለካከት ኢትዮጵያችን ከነበረችበት አጠቃላይ ሁኔታ ጋር የሚጋጭ ስህተተት ያለበት ብቻ ሳይሆን፣ በዛሬው የለውጥ ፍላጎታችን ላይ የሚረጨው ቀዝቃዛ ውሃ የራሱ መዘዝ ያለው ስለሆነ መታረም ይገባዋል::

ዛሬ ካለንበት አዘቅት የምንገኘውም፣ ስር ነቀል ለውጥ በማለማችን፣ ወይም አብዮት በማድረጋችን አይደለም ። የኢትዮጵያን ህዝብ ለለውጥ ያነሳሱት መሰረታዊ ጉዳዮች መልስ ባለማግኘታቸው እንጂ ። መፍትሄውም፣ የካቲትን ማውገዝ ሳይሆን፣ በየካቲት የጎደሉንን የድርጅትና አመራር ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ነው:: ከአብዮቱ መጨንገፍ፣ ከውድቀቱ በመማር፣ በተግባርም ይሁን በአስተሳሰብ መታረም ያለባቸውን ማስተካከያዎች ማድረግ ነው:: በ1966 መላው የሃገሪቱን ህዝብ አንገፍግፎ ለለውጥ ያነሳሳውን ትግል በማቀጣጠል በርካታ ኢትዮያውያን የከፈሉት መስዋእትነት ቀላል አይደለም:: በእዚያ ትግል ለወደቁት ሰማእታት የሚገባቸውን ክብር ሰጥተን የለውጥ ፍላጎታቸውንና ቁርጠኛነታቸውን ዛሬ ለምናደርገው ትግል መነሻ ማድርግ የግድ ነው:: የቀደምቶቹን የነጻነት የተጋድሎ ታሪክ፣ ለፍትህ ለእኩልነት የተከፈለ መስዋእትነት፣ እድገት ብልጽግንና ለማምጣት፣ አንድነትን በዴሞክራሲና በእኩልነት መሳሪያነት ለማጥበቅ የተጀመረን በአጭር የተቀጨ ረጅም ጉዞ ሰርዞ፣ ከስህተት ትምህርት የቀሰመ ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣትና አዲስ ታሪክ መስራት አይታሰብም:: ስለሆነም ዛሬ የየካቲት አብዮትን 35ኛ አመት ስንዘክር በዘመናቸው በሃገራቸው ላይ የነገሰውን ኋላ ቀርነት፣ የመብት እረገጣና ድህነት፣ ረሃብን፣ በሽታንና ውርደትን ለማስወገድ መስዋእትነት ለከፈሉት ወገኖች አድናቆታችንን በመግለፅ፣ የለውጥ ጥማታቸውን ተጠምተን፣ የመብት ረሃባቸውን ተርበን፣ የነፃነት ፈለጋቸውን ተከትለን፣ ከውድቀታቸው ተምረን፣ ለትውልዳችን የተላለፈውን ሀገርን ለጥሩ የመቀየር ህልማቸውን ከመረከብ ወደኋላ ማለት አይቻለንም ።

ዛሬም እንደ ትናንቱ፣ ዛሬም እንደ 35 አመት በፊቱ፣ ሃገራችን በለውጥ ወጀብ ውስጥ ትላጋለች ። እንደገና የለውጥ ቋያ የሚቀጣጠልበት ፍም እየጋመ ይገኛል ። በየካቲት 1966 በአለም ዙሪያ የነበረውን ቀውስ የሚያስንቅ፣ የኢኮኖሚ ቀውስ ተብዛዝቷል ። የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ በምዕራብ ደጓሚዎቹ እስትንፋስ አድሎአዊ አገዛዙን መቀጠል የሚችልበት ሁኔታ እየተዳከመ ይገኛል ። ተሸንፎ ከሱማሌ ተባሯል ። በየካቲት 1966 በኢትዮጵያ ውስጥ አንድም እንኳ የተደራጀ የፖለቲካ ፓርቲ አልነበረም ። ዛሬ በአስርተ የሚቆጠሩ የፖለቲካ ድርጅቶች ተመስርተዋል ። ከ35 አመታት ትግላቸውና ውድቀታቸውም ብዙ ተምረዋል ። የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት፣ ነገ የተሻለ ቀን እንደሚመጣ የሚያበስር ነው ። ወያኔ ከየካቲት አብዮት ሊማር በተገባው ነበር ። ሆኖም ፈቃደኛ አልሆነም ። ዛሬ የህዝብን ጥያቄ ተቀብሎ እንደ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ህጋዊ ሆኖ የመቀጠል ዕድል አለው ። አሻፈረኝ ብሎ፣ ሁለተኛ የካቲት ሲነሳ ግን ወደታሪክ ትቢያ ከመወርወር በቀር አማራጭ አይኖረውም ። ዛሬ የሚመካበትም ሰራዊት፣ ልክ እንደ ዛሬ 35 አመቱ፣ በህዝብ ላይ አልተኩስም ያለ ቀን፣ የዘረኞች ግብአተ መሬት ይሆናል ። ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ ነው ነገሩ ።

## ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።



የፖስታሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ሃይለ ሀሳብ

## የኢትዮጵያው መንግስት ሰራተኛ፡- ዋና ግፍ ቀማሽ እና ታላቅ የለውጥ ሃይል

*በተሰፋዬ ማሩ*

ከገበሬው ቀጥሎ የአገራችን የጀርባ አጥንት ሆኖ የሚያገለግለው የኅብረተሰብ ክፍል መንግስት ሰራተኛው ነው። ጥርስ እንደነቀልን "ሀ ሁ..."ን አስተምሮ፣ የኑሮ ዘዴን እና ሂሳብን አሰንቆ ለኑሮ ያዘጋጀን መምህር፤ ጓሮ ለጓሮ ባዶ እግራችንን ሮጠን ስንጫወት ሰባራ ጠርሙስ ቆርጦን ያገኘንን ቁስል አጥቦ ያሸገልን፣ እንዲሁም በበጋ ወቅት ያጠቃን ወባ ስር ከመስደዱ ፊት መድሃኒት ሰጥቶ ነፍሳችንን ያቆየልን ሃኪም፤ በቅርብ ጊዜ ታሪካችን አገራችን በባዕድ ጦር በተወረረች ጊዜ ተዋግቶና ተጋድሎ ድንበሯን ያስጠበቀው ወታደር፤ እና ሌሎችም መንግስት ሰራተኞች ናቸው። የመንግስት ሰራተኛው ውለታ ብዙ ነው። ነገር ግን፣ የመንግስት ዋና ግፍ ቀማሽ ከሆኑት የኅበረተሰባችን ክፍሎች ውስጥም አንዱ መንግስት ሰራተኛው ነው።

ከሌሎች የኅብረተሰባችን ክፍሎች የላቀ ዘመናዊ ትምህርትን የቀሰመና ስለ መብቱ የሚያውቅ ስለሆነ፤ እንዲሁም ደግሞ ቢተባበርና አቅሙን ቢያሰባስብ ታላቅ የለውጥ ሃይል ሊሆን እንደሚችል ስለሚታወቅ፣ አገራችንን ተፈራርቀው የገዟት አምባገነኖች ሁሉ መንግስት ሰራተኛውን ለማድከምና በቁጥጥራቸው ስር ለማዋል ብዙ ግፍ ፈጽመዋል። ዛሬም አምባገነኑ የነመለስ አገዛዝ ሰራተኛውን ማንገላታቱን ስራዬ ብሎ ተያይዞታል።

አምባገነኖቹ የህወሃት መሪዎች የስልጣንን ወንበር እንደተቆናጠጡ የመጀመሪያ ስራቸው ከፖለቲካቸው ጋር የማይስማሙ የዩኒቨርሲቲ መምህራንን በጅምላ ማባረር ነበር። ያኔ የጀመረው መምህራንን ከስራ የማፈናቀል አባዜ እስከ ዛሬ ቀጥሏል። በሌላ ፓርቲ አባልነት ተጠርጥረው በሃሰት ውንጀላ የሚታሰሩና የሚባረሩ፤ ስራ ለማግኘት ወይም ስራቸውን ለማቆየት ሲሉ፣ እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት ዕድል አግኝተው ዕድገት ለማግኘት ገዢውን ፓርቲ ለመቀላቀል የተገደዱ፤ በህዝብ ተመርጠው የወረዳ እና የቀበሌ አስተዳደር ስራ ከተረከቡ በኋላ የገዢው ፓርቲ አባላት ለመሆን ባለመፈለጋቸው ከስራቸው የሚወገዱ ዜጎች አያሌ ናቸው።

ተወልጄ ባደኩባት ወለጋ ዉስጥ በምትገኝ ትንሽ ከተማ ብቻ የተከሰቱ ብዙ ምሳሌዎችን አውቃለሁ። አንድ ለረጅም ጊዜ በኦነግ አባልነት ይጠረጠር የነበረ የሁለተኛ ደረጃ መምህሬ ከብዙ ስለላ በኋላ ማስረጃ ሊገኝበት ስላልቻለ የትምህርት ቤት ንብረት ሰርቀሃል በሚል ተወንጅሎ ወህኒ ቤት ተጨምሯል። የመንግስት ብድርና ቁጠባ ቢሮ ሃላፊ ሆኖ የመጣ ወጣት ልጅ ደግሞ ታሪኩን ለቤተሰቤ ሲያጫውት፣ ምንም ለመደበቅ ግድ ሳይለው፣ ትምህርቱን ሲጨርስ ስራ የማግኛ ብቸኛው መንገድ ኦህዴድን መቀላቀል መሆኑን ሲሰማ፣ እሱን በመቀበሉ አሁን የያዘው ስራ እንደተሰጠው ነግሮናል። ስለፖለቲካ ደንታ የሌለው የሁለተኛ ደረጃ የኬሚስትሪ መምህሬ ደግሞ ህንድ አገር ሄዶ ሁለተኛ ዲግሪውን ለመስራት ስለፈለገ ብቻ ኦህዴድን መቀላቀሉን አውቃለሁ።

የገዛ አጎቴ ሁለት ጊዜ የቀበሌ ሊቀመንበር እንዲሆን በህዝብ ተጠቁሞና ተመርጦ፣ የኦህዴድ ፓርቲ አባልነት ፎርም እንዲሞላ ተነግሮት ባለመቀበሉ ሹም ሽር እየተደረገ ከስራው ወጥቷል። ከዛ በኋላ ደግሞ በ1993 በተደረገው ምርጫ ለወረዳ ምክር ቤት አባልነት እንዲወዳደር ከፍተኛ ግፊት ደርሶበት ቢቀበልም፣ ምርጫው ሲቃረብ ኦህዴድን እንደሚወክል ተደርጎ መቅረቡ ግን በሱ እውቀትም ሆነ ፈቃድ የተደረገ አልነበረም።

ከምርጫ 97 ወዲህ እነዚህ ሁሉ ችግሮች ተባብሰው የገዢው ፓርቲ አባል ሳይኮን ሊገኙ የሚችሉ የመንግስት ስራዎች እየጠፉ ነው። አሁን ጊዜ ዘመዶቼን ጥየቃ ስልክ በደወልኩ ቁጥር የሚነገረኝ ስንቶች ስራ ፈልገው የኦህዴድ አባል ለመሆን እንደተገደዱ፤ ስንቶቹ ሰራተኞች የአባልነት ፎርም እንዲሞሉ ከፍተኛ ጫና እንደሚደረግባቸው እና የመሳሰሉትን ነው።

ስለ ፖለቲካ ጉዳይ ኖሯት የማያውቅ ጓደኛዬ ሁለተኛ ደረጃን ከጨረሰች በኋላ እንደ ብዙ የኢትዮጵያ ወጣቶች ስራ አጥታ በየዘመዶቿ ቤት እየተንከራተተች ለዓመታት ቆየች። በወንድሟ እርዳታ የመምህራን ማሰልጠኛ ገብታ ጨርሳ ስትወጣ ግን ስራ ለማግኘት  ግዴታ የኦህዴድ አባል መሆን እንዳለባት ግልጽ ስለተደረገላት የአባልነት ፎርም ሞላች።

በዛው ሰሞን ደግሞ ከሷ ቀድማ ለረጅም ዓመታት አስተማሪ የነበረች እህቷ፣ የምታስተምርበት ትምህርት ቤት ውስጥ አባል ሳትሆን የቀረችው እሷ ብቻ በመሆንዋ፣ አድሎ ተደርጎባት ወይ ከደሞዝ ዕድገት እንዳታጣ ወይም ከስራዋ ጭራሹኑ እንዳትባረር ፈርታ እያጉረመረመች አባል ሆነች። እንደ ፓርቲ አባል ደግሞ፣ እዚህ ግባ ከማይባል ደሞዛቸው በግዴታ የአባልነት ክፍያ መክፈል ይጠበቅባቸዋል።

በቅርብ ጊዜ ደግሞ ገዢው ፓርቲ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎችን የፓርቲው አባል ሳይሆኑ "አባል እንድትሆኑ ተመርጣችኋል" ብሎ እያስገደደ በወረዳና በቀበሌ ምርጫ ወክለውት እንዲወዳደሩ አድርጓል። በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥም ለውጥን በማምጣት ስም፣ ቢዝነስ ፕሮሰስ ሪኢንጂነሪንግ (ቢ.ፒ.አር.) ለማድረግ ግምገማ ሲያደርግ ቆይቷል። በሌሎች አገሮች ወይም የግል ተቋማት ውስጥ ቢ.ፒ.አር. ጥቅም ላይ የሚውለው ስራ በጥራትና በፍጥነት እንዳይሰራ የሚከለክሉ እንቅፋቶችን አስወግዶ መፍትሄዎችን ለመፍጠር ነው። ገዢው ፓርቲ ግን እየተጠቀመበት ያለው እሱን የማይደግፉትን ከስራ አባሮ በነሱ ምትክ አባል የሆኑትን ለመተካት ነው።

ከዘር ጋር በተያያዘም በመንግስት ተቋማት ውስጥ ግልጽ የሆነ አድሎ ይደረጋል። ይህ ችግር በተለይ በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ውስጥ በግልጽ ይካሄዳል። የኦሮሞ ድጋፍ ቡድን በመባል የሚታወቅ ድርጅት በ1998 ያነጋገረው የመከላከያ ሰራዊት አባል ይህንኑ መስክሯል። ዘነበ አድማሱ ይባላል፤ በአዋሽ አርባ ካምፕ የታንክ ነጂና አሰልጣኝ ነበር። በሰራዊቱ ውስጥ ከሚሰጠው እድገት ጀምሮ እስከሚታደለው ራሽን፣ ልብስ እና የማደሪያ ቦታ መብቶች ድረስ አድልዎ እንዳለ ገልጿል። በኦሮሞዎች የሚመሩ ትላልቅ ብርጌዶች ሆን ተብሎ ለስራቸው የሚያስፈልጓቸው ቁሳቁሶች እንዲዘገዩባቸው ሲደረግ፣ በአንድ ዘውጌ ማህበረሰብ አባላት ለሚመሩ ነገር ግን ከነሱ እጅግ ላነሱ ብርጌዶች ያለምንም ችግር ይሰጣል። በተጨማሪም፥ የዚሁ ዘውጌ አባላት የሆኑ ዝቅተኛ ስልጣን ያላቸው አባላት የመከላከያ ሰራዊቱ የአንድ ዘውጌ ማህበረሰብ ወይም የገዢው ፓርቲ ንብረት የሆነ ይመስል ከነሱ የላቀ ስልጣን ያላቸውን ኦሮሞዎች እንደሚያዙና እንደሚያመናጭቁ ተናግሯል። ስለሚደረገው አድልዎም ተቃውሞ የሚያሰሙ ኦሮሞዎች በኦነግ አባልነት ተወንጅለው እየተወሰዱ የት እንደደረሱ እንደማይታወቅ እና ይህ በገዛ ጓደኞቹ ላይ ጭምር እንደደረሰ ዘነበ አጋልጧል።

አገዛዙ በመንግስት ሰራተኞች ላይ የሚያደርሰው ግፍ በነዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም። ብዙ የመንግስት ሰራተኞች የስራ ውሳኔዎችን የሚያስተላልፉት በስራቸው መመሪያ እና በስልጠናቸው ላይ ተመስርተው ሳይሆን የገዢውን ፓርቲ ካድሬዎች ለማስደሰት ሲሉ ነው። ጥቃቅን ውሳኔዎችን እንኳ ካድሬዎችን ሳያማክሩ ለማስተላለፍ የሚፈሩ ብዙ ናቸው። እነዚህ ነገሮች ስራ ከማጓተታቸው አልፎ የሚተላለፉት ውሳኔዎች ብቃት በሌላቸው ሰዎች ጫና ብቻ የተፈበረኩ ስለሆኑ የጥራት ጉድለትንም ያስከትላሉ። ይህ ደግሞ በአገሪቱ ላይ ቀጥተኛ ወጪ ከመጨመሩም በተጨማሪ፣ ለሰራተኞቹ ሙያዊ እና ግላዊ እድገት አስፈላጊ የሆኑ እሴቶችን፣ ለምሳሌ፡- ውሳኔዎችን በነፃነት የማስተላለፍ ልምድ፣ እንዳያጎለብቱ ያደርጓቸዋል። ከዚህም የተነሳ ተስፋ ቆርጠው የራሳቸውንም ልምድ ለማዳበር እና አገርን የሚያሻሽል ስራ ከመስራት የሚቆጠቡ ብዙ ናቸው። ብዙዎችም አገር ጥለው ይሰደዳሉ። ያ ሁሉ ደግሞ መልሶ የሚጎዳው አገራችንን ነው፤ ምክንያቱም በልምድ የጎለበቱ ዜጎችን እንዳታፈራ ስለሚከለክላት።

የመንግስት ሰራተኞች በመደራጀት መብታቸውን ለማስከበር በዓለም አቀፉም ሆነ በኢትዮጵያ ህግ-መንግስት የተሰጣቸውን መብት እንዳይጠቀሙም ተደርጓል። ለዚህ እንደ ምሳሌ ሊጠቀስ የሚችለው የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ከአመራሩ መታሰር፣ መገደልና መሰደድ ጀምሮ ንብረቱ ተነጥቆ ለተለጣፊ ማህበር እስኪሰጥ ድረስ ግፍ ደርሶበታል። የኢትዮጵያ ጠበቃዎች ማህበር ደግሞ የቅንጅት መሪዎችን ኢ-ፍትሃዊ እና የጅምላ እስር እንደ ታላቅ የሰብዓዊ መብት ረገጣ ተመልክቶ ያለ ክፍያ ሊሟገትላቸው ተነስቶ ወያኔ/ኢህአዴግን ካስቆጣ ወዲህ ገዢው ፓርቲ ተለጣፊ ማህበር ከፍቶ ከስራ ውጪ ሊያደርገው እቅድ እንዳወጣ ይነገራል።

ይህንን የመሳሰሉት በመንግስት ሰራተኞች ላይ የሚደረጉ የመብት ረገጣዎች በዓለም አቀፍ ህግም ሆነ አገዛዙ እራሱ ባስጻፈው፣ ነገር ግን የተፃፈበትን ወረቀት ያህል እንኳ በማያከብረው ህገ መንግስት መሰረት ህገ-ወጥ ናቸው።

ኢትዮጵያ የተስማማችበት ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ ባጠቃላይ ስለሰዎች መብትና ስለስራ መብት ከሚለው የሚከተሉትን ቅንጭቦች እንመልከት፡- "አንቀጽ 1፡- የሰው ልጅ ሁሉ ሲወለድ ነጻና በክብርና በመብትም እኩልነት ያለው ነው፤ የተፈጥሮ የማስተዋልና ሕሊናው ስላለው አንዱ ሌላውን በወንድማማችነት መንፈስ መመልከት ይገባዋል። አንቀጽ 2፡- እያንዳንዱ ሰው የዘር፣ የቀለም፣ የፆታ፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የፖለቲካ ወይም የሌላ ዓይነት አስተሳሰብ፣ የብሔራዊ ወይም የኅብረተሰብ ታሪክ፣ የሃብት፣ የትውልድ ወይም የሌላ ደረጃ ልዩነት ሳይኖሩ በዚሁ ውሳኔ የተዘረዘሩት መብቶችንና ነፃነቶች እንዲከበሩለት ይገባል። አንቀጽ 20፡- ቁጥር 2፡ ማንም ሰው የአንድ ማህበር አባል እንዲሆን አይገደድም። አንቀጽ 23፡- ቁጥር 1፡ እያንዳንዱ ሰው የመስራት፣ የስራ ነፃ ምርጫና ለስራም ትክክለኛና ተስማሚ የአሰራር ሁኔታዎችና ስራም እንዳያጣ መብት አለው። ቁጥር 2፡ እያንዳንዱ ሰው ያለ አንዳች ልዩነት ማድረግ ለአንድ ዓይነት ስራ እኩል የሆነ ደመወዝ የማግኘት መብት አለው። ቁጥር 4፡ እያንዳንዱ ሰው ጥቅሞቹን ለማስከበር የሙያ ማህበሮችን ለማቋቋምና ማኅበርተኛ ለመሆን መብት አለው።"

የኢትዮጵያም ህገ-መንግስት እራሱ ኢትዮጵያዉያን ዜጎች በነፃነት የመስራት መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። ህገ-መንግስቱን የምጠቅሰው ያሉትን መረጃዎች አሰባስቦ ለማቅረብ ያህል እንጂ ኢህአዴግ ቁብ ይሰጠዋል ብዬ አይደለም። ለነገሩ የአገሪቱ ህገ-መንግስት ስለ ዜጎች መብት የሚናገረውን ለማክበር መንግስት አስቀድሞ ዜጎችን እንደ ዜጎች ማየት አለበት። ኢህአዴግ ግን ኢትዮጵያዉያንን መብቶች እንዳላቸው ዜጎች አያይም። ደግሞም ለራሱ ህገ-መንግስቱን እየሰበረ ህጋዊ እና ሰላማዊ ተቃውሞ የሚያደርጉን ዜጎች ግን ጸረ-ህገ መንግስት ብሎ በመፈረጅ ለህገ-መንግስቱ ያለውን ንቀት ከመግለጽም አልፎ ደጋግሞ አፊዞበታል።

ለማንኛውም ህገ-መንግስቱ ስለ ዜጎች እና ስለስራ መብቶቻቸው ከሚለው የተወሰኑ ቅንጭቦችን እንመልከት፡- "አንቀጽ 25፡- ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸው፤ በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በህግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል። በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ አመጣጥ፣ በሃብት፣ በትውልድ

ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው። አንቀጽ 31፡- ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማኅበር የመደራጀት መብት አለው። አንቀጽ 41፡- (1) ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሃገሪቱ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ስራ የመስራት መብት አለው። (3) የኢትዮጵያ ዜጎች ሁሉ በመንግስት ገንዘብ በሚካሄዱ ማኅበራዊ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብት አላቸው።" አንቀጽ 42 ደግሞ ሰራተኞች የስራና የኢኮኖሚ ሆኔታዎችን ለማሻሻል የመደራጀት መብት እንዳላቸው ይደነግጋል።

በአጠቃላይ ከነዚህ ድንጋጌዎች የምናገኘው ጭብጥ፡- ሰዎች በተፈጥሯቸው ነጻ እና እኩል እንደሆኑ፤ በዘር፣ በቋንቋ፣ በፖለቲካ አመለካከት እና በመሳሰሉት የተነሳ አድልዎ ሊደረግባቸው እንደማይገባ፤ ህጋዊ እስከሆነ ድረስ የመረጡትን ስራ የመስራት መብት እንዳላቸው፤ ስራን ጨምሮ በመንግስት ገንዘብ የሚካሄዱ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን የፖለቲካ አመለካከታቸው ወይም ዘራቸው ሳይገድባቸው በእኩልነት የመጠቀም መብት እንዳላቸው፤ የአንድ ማህበር ወይም ቡድን አባል ለመሆን መገደድ እንደሌለባቸው፤ እና ጥቅማቸውን ለማስከበር የመደራጀት መብት እንዳላቸው ነው።

በኢትዮጵያ ግን፥ ከላይ የተዘረዘሩት ግፎች እና ህጎቹ ሲወዳደሩ ያልተሰበረ ህግ እና ያልተደፈረ መብት የለም። በፖለቲካ ለመሳተፍ ፍላጎት የሌለው፤ ዝም ብሎ ስራውን ሰርቶ እራሱንና ቤተሰቡን ለመደገፍ፣ በሙያው ለማደግና አገሩን ለማገልገል የሚፈልገው ዜጋ ያንን ማድረግ እንደማይችል ባገዛዙ ግልጽ ተደርጎለታል። የፓርቲ አባል ሆኖ መዋጮ ካልከፈለ፤ የሙያው ስነምግባር ከሚፈቅድለት ውጪ የአንድን ካድሬ ፍላጎት ለማሟላት ሲል ውሳኔ ካላስተላለፈ፣ መንግስት ሰራተኛው በገዛ አገሩ ሰርቶ ለመብላትና በሰላም ለመኖር አይፈቀድለትም።

እንደ ኢትዮጵያ ባለች ድሃ አገር የተገኘው ምሁር፣ ስልጠናና ልምድ ያለው ዜጋ ሁሉ ተሰብስቦ አመቺ በሆነ እና ከአድልዎ እና ካላስፈላጊ ጣልቃ ገብነት ነፃ በሆነ ሁኔታ አገሪቱን በማልማት ስራ ላይ ማተኮር ሲገባ፤ በወያኔ/ኢህአዴግ የሚመራው ገዢ መንግስት ግን የአጭር ጊዜ የፖለቲካ ጥቅም ለማግኘት የአገሪቱ የጀርባ አጥንት እና የወደፊት ተስፋ የሆነውን መንግስት ሰራተኛውን የመስበር ስራውን ተያይዞታል። በዚህም ተግባሩ የአገሪቱን ኢኮኖሚ ከድጥ ወደማጡ እየወሰደና የረጅም ጊዜ ጥቅሟን አደጋ ላይ እየጣለ ነው።

ይህ ሁሉ አፈና ዲሞክራሲ ባለበት እና የግለሰብ መብት በሚከበርበት አገር ባልኖረ ነበር። ዲሞክራሲያዊ በሆኑ አገሮች የዜጎች ሰብዓዊ መብት መከበር ሰው በተፈጥሮው ሊያገኘው የሚገባው ነገር ብቻ ሳይሆን ለኢኮኖሚ እድገትና ለኅብረተሰቡ ስልጣኔ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ተደርጎ ነው የሚታየው። ምክንያቱም ዜጎች የመረጡትን ስራ የመስራትና በነፃነት የማሰብ መብታቸው ሲከበር፣ በርትተው በመስራትና የፈጠራ ስራዎችን በማፍለቅ ለኅበረተሰቡ መሻሻል አስተዋጽኦ ከማድረጋቸውም ባሻገር ለራሳቸውም የግል ተጠቃሚዎች እንደሚሆኑ ስለሚረዱ፣ በየፊናቸው ለመትጋት ያላቸው ፍላጎት እንደሚጨምር ግልጽ ስለሆነ ነው።

ስለዚህ የኢትዮጵያው መንግስት ሰራተኛ ይህ አገዛዝ በህይወቱ፣ በመብቱ፣ በእድል ፈንታው እና በራሱና በልጆቹ ተስፋ ላይ ሲያፌዝ እያየ ምን ማድረግ አለበት? ይህ ማህበረሰብ ካለው ንቃተ-ህሊና አኳያ እጁን አጣጥፎ መቀመጥን እንደ አማራጭ የሚወስድ አይመስለኝም። ለዚህም ነው እስከ አሁን ድረስ በአገራችን ውስጥ የተዳከሙም ቢሆኑ ያሉትን የዲሞክራሲ ደጋፊ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እና ሌሎች ድርጅቶችን በዋናነት ደግፎ ያለው መንግስት ሰራተኛው የሆነው። ለዚህም ነው በአገዛዙ ዓይን ሁሌም በጥርጣሬ የሚታየውና የሚፈራው።

ነገር ግን በአገራችን ለዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበር በሚደረገው ትግል ተጨባጭ ለውጥን ለማምጣት መንግስት ሰራተኛው ተሳትፎውን በእጥፍ ድርብ መጨመር አለበት። አምባገነኖቹን የሚያርበደብደው የመንግስት ሰራተኛው እምቅ ሃይል እሳት መለኮስ አለበት። የመደራጀት መብትና የመሳሰሉት መብቶች መታፈን፣ ባለው ከፍተኛ እውቀት አገሪቱን የመምራትና የማስተዳደር ተስፋ ለተጣለበት እንደ መንግስት ሰራተኛው ላለ የኅብረተሰብ ክፍል፣ እጅን አጣጥፎ ለመቀመጥ እንደ ሰበብ መቆጠር የለበትም።

መንግስት ሰራተኛው የፈጠራ ሃሳቦችን በመጠቀም ለራሱም ታግሎ ህዝቡን ሊያታግል ይችላል። በተለይም ካለው እውቀት አኳያ ህዝቡ ስለ መብት ያለውን እውቀት በማሻሻል እና የማያውቁትን በማስተማር በኩል ትልቅ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል። እነዚህ ስራዎች ግዴታ ትላልቅ ስብሰባዎችን በመጥራት የሚካሄዱ ሳይሆኑ ከሚታመኑ ጎረቤቶችና የቤተሰብ አባላት ጋር ቡና ሲጠጣ በሚደረጉ ውይይቶች፤ ከጸሎትና ከመጽሃፍ ቅዱስ ጥናት በኋላ በሚደረጉ ውይይቶች፤ በመምህራንና በተማሪዎች መካከል በሚደረጉ የአንድ ለአንድ ግንኙነቶችና በመሳሰሉት የሚደረጉ ሊሆኑ ይችላሉ።

ከዲሞክራሲ ሃይሎች ለሚደረጉ ጥሪዎች መልስ በመስጠት እና ከነሱም ጋር በመተባበር ሊያበረክተው የሚችለው አስተዋጽኦም ከፍተኛ ነው። በዚህ አኳያ በግዳጅም ሆነ በግዴታ የገዢውን ፓርቲ ተቀላቅለው በአስተዳደር ስራ ውስጥ ተሰማርተው ያሉ እና ከአገዛዙ የግፍ ስራ ጋር መተባበር የማይፈልጉ ዜጎች፣ የአገሪቱንና የዜጎችን ደህንነት የሚጎዱ የሚስጥር እቅዶቹን አስቀድመው ለዲሞክራሲ ሃይሎች በማሳወቅ፤ እንዲሁም በየፊናቸው የግፍን ስራ እንዲሰሩ ሲጠየቁ እምቢ ብለው ለአገዛዙ መንግስት ድጋፍን በመከልከል አፋኙን መንግስት ከውስጥ እንደ ብል እየቦረቦሩ የውድቀቱን ቀን ለማፋጠን ይችላሉ።

ባጠቃላይ፥ የኢትዮጵያው መንግስት ሰራተኛ እራሱን ከግፍ ቀማሽነት አውጥቶ መብቱን ለማስከበር ያለው ዋነኛ መሳሪያ የራሱ እምቅ ሃይል ነው። ያንን እምቅ ሃይል ከተቀበረበት አውጥቶ ስራ ላይ ካላዋለ፣ ከዚህ የባሰ የመብት ረገጣን እና ሰቆቃን ሊጠብቅ ይገባዋል እንጂ ሁሉም ከመሬት ተነስቶ ይሻሻላል የሚል ተስፋ ሊኖረው አይገባም። "ያልሰራ እንደማይበላ" ከማንም በላይ መንግስት ሰራተኛው ያውቃል። እንግዲያውስ ያልታገለ መብቱ እንደማይከበርለትም ግልጽ ሊሆንለት ይገባል።

## የመለስ ዜናዊ ... (ከገጽ 1 የዞረ)

የግንቦት ሰባት ድምጽም ይህ አነጋገሪ በሆነው የመለስ ዜናዊ ቃለ ምልልስ ዙሪያ መለስ ዜናዊንና ኢህአዴግ የሚባለውን ድርጅት በሚገባ የሚያውቁትን የግንቦት 7 አመራር አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ አስተያየታቸውን እንዲሰጡን ጠይቀን ነበር።

እውነት መለስ ዜናዊ ከህላፊነቱ ሊለቅ ይችላልን፤ ነበር የመጀመሪያ ጥያቂያችን ‹‹ በቅድሚያ ይህን የመለስ ዜናዊ ወሬ ዜና ሆኖ መቅርብ የሌለበት ተራ ነገር ነው። መለስ ዜናዊ ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን እንዳይቀጥል የሚወስነው ድርጅቱ ነው ሲል፣ ከመለስ ዜናዊ ፍላጎትና ትእዛዝ ውጭ የሚነቃነቅ፣ የራሳቸው ህሊናና ስብእና ያለቸው የአመራር አባላት የተሰባሰቡበት ኢህአዴግ የሚባል ድርጅት እንደሌለ ያውቃል። መለስ የፈለገው ሃገሬውንና አለምአቀፍ ህብረተሰቡን ለማወናበድ፣ ይለቃል አይለቅም በሚል ተራ ወሬ ሁላችንም እንድንጠመድ እርሱ ግን ያሻውን ወንጀል በርጋታ መፈጸም የሚችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር ነው። ከአባባሉ እንደምንረዳው ያው ኢህአዴግ ማለት እኔ ስለሆንኩ፣ ውሎ አድሮ እኔው ወስኜ ድርጅቴ ቀጥል ስላለኝ ያለፍላጎቴ ለድርጅቴ ስል እቀጥላለሁ እንደሚል አስቀድሞ እየነገረን ነው።

መለስ ዜናዊ በሃገራችን ደህንነትና ጥቅም ላይ የፈጸመውን ወንጀል እያወቀ፣ በኦጋዴን በወገኖቻችንና በሱማሌ ህዝብ ላይ በፈጸመው ጸረ- ህዝብና የጦር ወንጀል በአለም አቀፉ ፍርድ ቤት እንደሚከሰስ እያወቀ፤ በሁሉም ኢትዮጵያውያን ላይ የፈጸመው ግፍ ሃገሩን በሚያቃጥልበት ሰአት ሰልጣን ይለቃል ማለት የማይታሰብ ነው። ይህንን የመለስን ተረት ተረት የግንቦት 7ድምጽ ከቁም ነገር ወስዶ ግዜውን ባያጠፋበት ይሻል ነበር። መለስ ከስልጣን የሚወርደው ከርሱ በፊት እንደነበሩት ገዡዎች አንገቱን ታንቆ ብቻ ነው። ›› ብለውናል።

በዚሁ አጋጣሚ አንዴ ከጀመርነው አይቀር በማለት አቶ አንዳርጋቸውን መለስ ዜናዊ የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር በሆኑት በወይዘሪት ብርቱካን መታሰር ላይ በሰጠው አስተያየት ላይ የራሳቸውን አስተያየት እንዲያክሉበት ጠይቀናቸው ነበር። ‹‹ መለስ ዜናዊ ብርቱካን ሚደቅሳን በእድሜ ልክ እስራት ቃሊቲ የወረወራት ህግ ነው ሲል አድምጨዋለሁ። ግን ማወቅ ያለብን ቀደም ብየ፣ መለስ ማለት ኢህአዴግ ኢህአዴግ ማለት መለስ ነው እንዳልኩት፤ በተመሳሳይም በኢትዮጵያችን ከመለስ ዜናዊ ፈቃድ ውጭ የቆመ የህግ ተቀዋም፣ የህግ ሂደት፣ ህግና ህገ መንግስት የለም። በኢትዮጵያ ህግ ማለት መለስ ዜናዊ ማለት ነው። መለስ ብርቱካን በህግ መሰረት ታስራለች ሲለን በእኔ በመለስ ፍላጎት ታስራለች ማለቱ ነው። እኔም የማምነው ይህንኑ ነው። ሌላው ሁሉ መለስ ስለ ህግ የበላይነትና ስለ ህግ ሂደት የሚያወራው ተራ ማጭበርበር ነው። ከመለስ ፍለጎት ውጭ፣ ህግ አለ ብለው የሚያስቡ ጀሌዎቹና ለጥቅማቸው የቆሙ ሃይሎች መለስን ሊያምኑት ይችላሉ። የኢትዮጵያን ህዝብ ግን ማሳመን አይቻልም። ችግሩ ግን አማባገነኖች በሙሉ የአእምሮ በሽተኞች ስለሆኑ መለስ ለሌላው ማጭበርበር ባዘጋጀው ውሸት እራሱን ሊያሳምን ይችላል። አምባገነኖች ራሳቸው የፈጠሩትን ልብ ወለድ አለም በእውነተኛው አለም ምትክ ተክተው የሚኖሩ ስለሆነ መለስ ዜናዊ ከርሱ ፍለጎት ውጭ ህግ እንዳለ አምሮ ሲናገር ብንሰማው ታሟልና ልንገረም አይገባንም። አደገኛው ነገር እንደህ አይነት በሽተኛ ፍጥረት የ80ሚሊዮን ዜጎች እጣ ወሳኝ ሆኖ መለቀቁ ነው።

በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተውናል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ ለውጥ አድርጓል።**

በዚሁ መሰረት ከአሁን ቦኋላ **በ7485 KHZ በ41 ሜትር ባንድ** እና **በ9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።